# ኑሮና መኖር የተወደደበት ህዝብ!!

*************************

ይህ አባባል የደደቢት ሚዲያው ዶ/ር ሃይለ ወይም የትግራይ ሚዲያ ሃውሱ ስታሊን ገ/ስላሴ ወይም የርእዮቱ ቴዎድሮስ ፀጋዬ ከዚህ በፊት ሲጠቀሙበት ሰምቻለሁ። እርግጠኛ ስላልሆንኩኝ ከሶስቱ አንዱ ሳይሆን ቀርቶ እና ሌላ ሰው ይጠቀምበት ከነበረ በቅድሚያ ይቅርታ እጠይቃለሁ!! አባባሉ እጅግ ስለተስማማኝ፣ በውሰትም ቢሆን መጠቀሙ አይከፋምና እውቅናውን ለሚገባችሁ ሰዎቼ ትንሽ እናውጋ!! ትንሽ ጊዜ ሲኖረኝ ዘርዘር ያለ ትዝብቴን አጋራለሁኝ!!

ከ14/06/2022 ጀምሬ ለተወሰኑ ቀናት ኑሮ ከተወደደበት ህዝብ መሀል ሁኜ፣ አዲስ አበባን የቻልኩትን ለመቃኘትና ለመታዘብ ሞክሬ ነበር! ከአዲስ አበባ ለበባና ኑሮ ከተወደደበት ህዝቧ ስገናኝ አንድ ዓመት ከሦስት ወራት አከባቢ ሁኖኛል። የከተማዋን መሬት እንደረገጥኩኝ፣ ኮንትራት ታክሲ ያዝኩኝና፣ ግራ ቀኙን እያማተርኩኝ ጉዞየን ቀጠልኩኝ። መጀመሪያ ተጋሩ በብዛት አገኝበታለሁ ብየ ወዳሰብኩት 22 አከባቢ ተጓዝኩኝ። ቦታው ላይ ደርሼ ከታክሲው ስወርድና ሂሳብ ለመክፈል እጄን ወደ ኪሴ እየከተትኩኝ "ሒሳብ ስንት ነው?" ስል አሽከርካሪውን ጠየኩት። እሱም ወዲያው ተቀብሎ 350ብር አለኝ። ትንሽ ግራ ተጋብቼ እና ጆሮየን ተጠራጥሬ "ስንት አልከኝ?" የሚል ጥያቄ ደግሜ ወረወርኩኝ። 350 ሲል እሱም ደግሞ ስለመለሰልኝ፣ ሳላመነታ የተባልኳትን ብር ቆጥሬ ሰጠሁት። ከዚህችው ተመሳሳይ መነሻ እና መድረሻ ከ120 — 150 ብር ነበር ከዚህ በፊት እከፍል የነበረው። እንግዲህ በቅፅበትና ሳይታወቀኝ ኑሮ ከተወደደበት ህዝብ መካከል አንዱ ሁኜ ለጥቂት ቀናት የምቀይባትን ጀልባ ላይ መሳፈሬን ገባኝ!!

22 አከባቢ ሁሌም ደመቅ ያለና በብዛት ተጋሩ የሚገናኙበት ሰፈር ነው። አሁንም እንደ ከዚህ ቀደሙ በብዛት ባይሆንም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ተጋሩ አሉ። ወዲያው ከታክሲ ወርጄ፣ የወንድሜ ልጅ የሆነችው ቆንጆ በምታንቀሳቅሰው ምግብ ቤት እንደገባሁኝ፣ ታላቁ ጓደኛና ወንድም ሙ. ተን ጨምሮ በርካታ ተጋሩ አገኘሁኝ። እነሱ መኖር ስለተወደደበት የትግራይ ህዝብ ሁኔታ፣ እኔም ኑሮ ስለተወደደበት የአዲስ አበባ ህዝብ ሁኔታ ለማወቅ እየተጠያየቅን ሰፊ ጊዜ ወሰድን። በየደቂቃው መብሉም መጠጡም በየዓይነቱ ይቀርብ ነበር።

በዚህ መሃከል ታላቁ ወንድሜ፣ ታናሸዋ እህቴ እና ባለቤትዋ ስለተቀላቀሉን፣ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ተቃቅፈን ናፍቆታችንን ተዋጣን። ገና ታናሽ እህቴን ላይ ውስጢ የመረበሽ ስሜት ቢሰማኝም፣ ስሜቴን ዋጥ አድርጌ ከሷና ባለቤቷ ጭዋታችንን ቀጠልን!! ለጊዜው ስለአጠቃላዩ ህዝብ ማውራት አቁመን፣ እነሱ ትግራይ ስላለው እኔም አዲስ አበባ ስላለው ቤተሰብ አንድ በአንድ እያነሳን አወራን። እስርቤት ገብተውና ተጋሩ በመሆናቸው ለስታገረ ወንድሜን ጨምሮ ሌሎች የቤተሰቡ አባላት አወጋን። ታናሸዋ እህታችንና ሌሎች የቤተሰቡ አባላት፣ የታሰሩትን ለማስፈታትና ለመጠየቅ ያሳለፉት ውጣ ውረድ በዝርዝር አዋረጁኝ። ፊታቸው ላይ ሁሉም ዓይነት ስሜት አነበብኩኝ!! የስኳር በሽታ

ታማሚ የሆነው ወንድሜ፣ የት እንደታሰረ ሳይታወቅ ቆይቶ ከሳምንት በኋላ ቦታው ቢታወቅም ምግብና መድሃኒት ተከልክሎ እግሩ ቆስሎ አደገኛ ደረጃ ላይ እስኪደርስ ያሳለፈበት የእስርቤት ቆይታው እንዲሁም ህመሙ ከፊቱ ይታይ ነበር፡፡

ከሁሉም ያገኘሁዋቸው ተጋሩ እና ወንድም እህቴ የተረዳሁት ነገር ቢኖር፣ አሁንም ከፍተኛ የደህንነት ሥጋት ውስጥ ስለመሆናቸው ነው፡፡ የከተማዋ የመንግስት ፀጥታ አካላት እንዴት እንደ ኤቲኤም ማሽን እንደተጠቀሙባቸው፣ ምን ያክል ጉዳት እንዳደረሱባቸው፣ አሁንም እንደፈለጉ ሰውን እያሰሩና እያሰቃዩ እንዳሉ በዝርዝር ነገሩዉኛል፡፡ በተለይ ተጋሩ ይበዙባቸዋል የተባሉ እንደ 22 ዓይነቱ ሰፈሮች፣ የመንግስት ሀይሎች የሴሊት ዳሰሳ በማካሄድ እንደሚያስሩ፣ እንደሚያንገላቱና ንብረት እንደሚዘርፉ ገልጸውልኛል፡፡ ብዙዎቹ እንደ ምክር ቢጤ ጣል ያደረጉልኝ ነገሮች፣ እዛው አከባቢ አልጋ እንዳልይዝ፣ ለማንም ከትግራይ መምጣቴ እንዳልናገር፣ በርካታ የድህንነት ሰዎች (ኤርትራውያን ጨምሮ) በአከባቢው እንዳሉና አላስፈላጊ ንትርክ ውስጥ መግባት እንደሌለብኝ ነበሩ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእህቴ ባለቤትን ጨምሮ በርካታ ያገኘሁዋቸው ተጋሩ በማንነታቸው ብቻ ከሥራቸው ተሰናብተው እንዳሉ እና ለከፋ ችግር ተጋልጠው እንዳሉ ተረዳሁኝ፡፡ እነዚህ ስጋቶችና የነሱ ልምዶች ከግምት ውስጥ አስገብቼ ሳስበው፣ መሃል አገር ያሉ ተጋሩ እንደ ትግራይ ያለው ህዝብ “መኖር እንደተወደደባቸው” ተረዳሁኝ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህ ተጋሩ እንደ ከተማዋ ነዋሪዎች “ኑሮም ተወደባቸዋል”!! ኑሮና መኖር የተወደደበት ሁለት ዓይነት ህዝብ በአገሪቷ እንዳለ ባውቅም፣ የከፋው ሆኖ ያገኘሁት ግን ሁለቱም የተወደደባቸው ተጋሩ መኖራቸው ማየቴ ነው!!!!

ጊዜው በመመሸቱና ድካም ቢጤ ስለተሰማኝ ሂሳብ ከፍለን አረፍ ወደ ምልበት ሰፈር ከወንድሜ፣ እህቴ እና ባለቤቷ ጉዞ ጀመርን፡፡ የተከፈለው ሂሳብ ከምታስቡት በላይ እጅግ ብዙ ነበረ!! የዛሬ ዓመት 20 — 50 ብር የነበረው ቢራ እጥፍ መጨመሩ፣ ሽሮና ጥብስም እንዲሁ በእጥፍ ዋጋቸው አድጎ አየሁኝ!! እውነቱም የአዲስ አበባ ህዝብ ኑሮ እንደተወደደበት በተግባር አየሁኝ!!

ወደ እማድርበት ሆቴል ስጓዝ ዓይኔ ቀኝና ግራ እያማተርኩኝ ትዝብቴን ቀጠልኩኝ፡፡ አዲስ አበባ የንግድ እንቅስቃሴዋ እንደተዳከመ የሚያሳዩ ምልክቶች አየሁኝ! እኔ የማውቃት አዲስ አበባ የሰው ትርምስ የበዛባት፣ በየመንገዱ የእለት ጉርሳቸው ለማግኘት ከዚህም ከዚህም የሚሯሯጡባት እና ህይወት ያለባት ከተማ ነበረች፡፡ አሁን ያለችው አዲስ አበባ እጅግ የቀዘቀዘች እና ሂይወት አልባ ነች! ይህ መቀዛቀዝ የገንዘብ ዝውውር እና በልቶ ለማደር የሚደረገው ሩጫ መቀነስ የሚያሳየው ከተማ ውስጥ ከባድ እንደሚያደርገው ግልፅ ነው!! ይህን ከግምት ውስጥ አስገብተህ ስታየው እውነትም በከተማዋ ኑሮ የተወደደበት ህዝብ አለ ያስብላል!!

ሌላው ስጓዝ ያየሁትና ኑሮ የተወደደበት ህዝብ እንዳለ የተገነዘብኩበት አጋጣሚ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት በየፌርማታው ያየሁት የሰው ሰልፍ ነው!! ከዚህ በፊትም ታክሲ ለመያዝ ሰልፍ እንደነበረ ባውቅም፣ አሁን ያየሁት

ግን ከመርዘው የተነሳ ለመመልከትም ይታክታል!! በተለይ አነስተኛ ክፍያ የሚያስከፍሉ የአውቶብስ ፎርማታዎች፣ ከዚህ በፊት አይቸው በማላውቅ መልኩ እጅግ ፈጅም ነበር!! ይህንን ዓይነቱ ትእይን ከተማዋ ኑሮ በተወደደበት ህዝብ ተሞልታ እንዳለች ተገነዘብኩኝ!!

አሲቤርጎ የምይዝቦት ቦታ ደርሼ ክፍል እንዳለ ከጠየቅኩኝ እና እንዳለ ከተነገረኝ በኋላ ቅድሚያ ሂሳብ 1100ብር ከፍየ ወደ ማደርያ ክፍሉ ዘለቅኩኝ፡፡ ክፍሉ ንፁህና ሰፊ ቢሆንም፣ መፀዳጃ ቤቱ ግን እጅግ ጠባብና ብዙዎቹ የክፍሉ እቃዎች የተሰበሩ ናቸው፡፡ መኖሪና ሽራ እንዳስሳሰ የማርፍባቸው ሆቴሎች፣ አሁን ከያዝኩት ክፍል ይበልጡ እንደሆነ እንጂ አያንሱም፡፡ የዋጋ ልዩነታቸው ግን የትየለሌ ነው፡፡ አሁን የያዝኩት ሆቴል ሂሳብ፣ መኖሪና ሽራ እንዳስሳሴ የ8ና 10 ቀን ወጪየ ነው!! እውነትም የአዲስ አበባ ህዝብ ኑሮ እንደተወደደበት የሚያሳይ አጋጣሚ አድርጌ ወሰድኩት፡፡

በነገታው የታደሰው ፓስፖርቴ ለመውሰድና የባንክ ሂሳቤን ለማስተካከል ወደ ተለያዩ ቦታዎች መጓዝ ነበረብኝ፡፡ ጉዞው ከሰሜን ምስራቅ የከተማዋ አከባቢ ጀምሬ፣ ሳሚት - መገናኛ - ሃያሁለት - ካዛንችስ - አምባሳደር - ጥቁር አንበሳ - ፒያሳ በማቋረጥ ተጓዝኩኝ፡፡ የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚንስቴር ስደርስ ግን ለየት ያለ ፅሁፍ አየሁኝ! ከንግስተ ሳባ ሆቴል ከፍ ብሎና ከውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚንስቴር ፊት ለፊት ባለው ህንፃ ያየሁት TDF የሚል ፅሑፍ ትግራይ በየጎደናው የማየውን ፅሁፍ አስታወሰኝ፡፡ ልዩነቱ ትግራይ ያለው ፅሁፍ ደቃቅ ሲሆን በዚሁ ቦታ ያየሁት ግን እጅግ ግዙፍ መሆኑ ነው!! ይህ ፅሁፍ ከዚህ ቀደም ደብዛዛ ቀይ መደብ ላይ በጥቁር ቀለም በደቃቅ ፊደሎች ተፅፎ እንደነበር ትዝ ቢለኝም አሁን ያለው ግን በአረንጓዴ መደብ ላይ በጥቁር ቀለም በግዙፍ የተጻፈ እና የቅርብ እንደሆነ ለመገመት ችያለሁ፡፡ የገረመኝ ግን ማለር የማይሰለቸው መንግስት እንዴት የTigrai Defense Force አህፅሮተ ቃል ተጠቅመሃል ብሎ ለውየው አለሮና የንግድ ተቋሙ እንዳልዘጋው ነው!!

እንደዚህና ሌሎች የከተማዋ ገፅታዎች እየታዘብኩኝ፣ የታደሰውን ፓስፖርቴ ለመውሰድ ከእልሌ ሆቴል ከፍ ብሎ ወደ ሚገኘው ፖስታ ቤት አመራሁኝ፡፡ ከቦታው እንደደረስኩኝ፣ ሁለት ሰዎች ቀድመውኝ ደርሰው ስለነበር እኔና እነቴ ሰዎቹ ተከትለን አግዳሚ መንበር ላይ ወረፋ ያዝን፡፡ ከአንዲት ወደ 60 ዓመት እድሜ የሚገመቱ ሴት በስተቀር ዘበኛው፣ ገንዘብ ተቀባዩዋና ፓስፖርት እያየ የሚሰጥ ሰውየ ሁሉም ኦሮምኛ ተናጋሪ ናቸው፡፡ እውነት ለመናገር ግን መስተንግዷቸው በጣም ፈጣን እና በትህትና የተሞላ ነበር፡፡

እዚህ ጋር አንድ ነገር ልንገራችሁ፤ ለአዲስ አበባ ህዝብ ኑሮ አለተወደደበትም የምታስብል አንዲት ነገር ታዘብኩኝ፡፡ እሱም ፓስፖርት ለማሳደስ የምትሰጠው የቀን ቀጠሮ እና የታደሰ ፓስፖርት ለመውሰድ የተዘረጋው ስርዓት ከዚህ በፊት ከነበረው እጅግ አጥሮና ትርምሱ ቀንሶ አግኝቼዋለሁ፡፡ እስከ 3ና - 4 ወር ይፈጅ የነበረው የእድሳት ጊዜ ወደ 1 ወር ወርዷል፡፡ የታደሰው ለማስደል ደግሞ ሁሉም ፖስታቤቶች የተገልጋዩን ስም የመጀመሪያ ፊደል ታሳቢ

በማድረግ ተደልድለዋል፡፡ ለምሳሌ ሥምህ በA የሚጀምር ከሆነ ዋናው ፖስታ ቤት፣ በW የሚጀምር ከሆነ ካዛንችስ ፖስታ ቤት  በD የሚጀምር ከሆነ ፒያሳ ያለው ፖስታ ቤት፣ ወዘተ በመሄድ ትወስዳለህ፡፡ ይህ ጉዳይም ስራና የከተማዋ ነዋሪዎች ኑሮ ሲያቀል የሚችል ማሳያ ተግባር አድርጌ መዝግቤዋለሁ፡፡ ይህን ስል ግን ሙሉ ማሳያ እንዳልሆነ ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፤ ምክንያቱም ፓስፖርት ለማሳደስ ይከፈል የነበረው 300 ብር አሁን በእጥፍ ጨምሮ 650 ብር መክፈል ግድ ስለሚል ነው፡፡

ፖስታ ቤቱ ጋር የነበረኝ ስራ እንደጨረስኩኝ፣ እህቴና ወንድሜ የታመመችና ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የተኛችውን የአክስታችን ልጅ ለመጠየቅ ጥቁር አንበሳ አስወርደን፣ እኔና የእህቴ ባለቤት ፒያሳ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተጓዝን፡፡ ንግድ ባንኩ ተገልጋዮች እንደ አዲስ መረጃቸው እንዲያስመዘግቡ ባወጣው መመሪያ መሰረት እኔም ተገቢውን መረጃ ሰጥቼ፣ የሞባይልና ኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎቶች ለመጠቀም የሚስችሉኝ ኮዶችች ፊልሜ ወጣሁኝ፡፡

ባንክ ጋር የነበረኝ ስራ እንደጨረስኩኝ ተመልሰን ወደ ጥቁር አንበሳ ሄድን፡፡ መኪናችን ከኢሚግሬሽን ወደ ተክለሃይማኖት በሚወስደው መንገድና የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መግቢ በር ትዩዩ አቁመን ወደ በሩ በእግር ተጠጋን፡፡ የሆስፒታሉ መግቢያ የሚጠብቁ ፖሊሶች በጥቁር ቀለምና በአማርኛ ሥማቸው የተጻፈበት ግራጫ ሹራብ ከላይ የደረቡ ሲሆኑ፣ ደብዘዝ ያለ አረንጓዴ ሱሪ ከታች ለብሰዋል፡፡ አብዛሃኞቹ ወጣቶች ሲሆኑ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች መሆናቸው ከስማቸው ማወቅ ይቻላል፡፡ እዚህ ጋር የገረመኝ ነገር ቢኖር፣ በሩ ላይ የቆመው ህዝብ ፎቨር ወደ የፖሊሶቹ ይሁንታ ለማግኘት በሚመስል መልኩ፣ በኦሮሚኛ ፖሊሶቹ ለማናገር ያደርግ የነበረውን ጥረት ነው፡፡  እህቴና ወንድሜ ከተወሰነ ደቂቃ በኃላ ተቀላቀሉን እና ለምን እንደዘገዩ ስጠይቃቸው የሰጡኝ መልስ የሚገርም ነበር፡፡ መግባት አይፈቀድም ተብለው ለበርካታ ደቂቃዎች እየለመኑ እንደቆዩ እና በስንት መለማመጥ 100ብር ለአንድ ሰው ከፍለው እንደገቡ ነገሩኝ፡፡ እንግዲህ አስቡት ዘበኞቹ አለምንም ፍርሃትና ይሉኝታ ከአንድ ሰው 100ብር ይቀበላሉ፣ መክፈል የቻለ እየከፈለ ይገባል ካልቻለ ከበር ይመለሳል፡፡ በእርግጥም የአዲስ አበባ ህዝብ ኑሮ ተወዶበታል ያስብላል!!

በጥቁር አንበሳ መግቢያ በር ላይ የታዘብነውን በየፊናችን እያሰላሰልን የመኪናችን አቅጣጫ ቀይረን፣ የቴሌ ዋና መስሪያቤት ተሻግረን፣ የዩኒቲ ፓርክ ወደ ግራ ይዘን፣ ሻራተን አዲስ በቀኝ በኩል እያየን ቤተሰብ ጥየቃ ጉዟችን ወደ ሃያ ሁለት አደረግን፡፡ ከሸራተን አዲስ ወደ ቤተመንግስት በምትወጣበት ወቅት፣ የችሎዉን የህዋ ምርምር ማእከል ዲዛይ ኮፒ ተደርጎ የተሰራ አዲስ ህንጻ፣ UNITY PARK የሚሉት ቃላት ለያንዳዱ ፊደል ወደ አንድ ሜትር የሚጠጋ የብረት ቅርፅ ተሰርቶለትና በትልቁ ለየብቻ የተሰቀለ ፊደል፡ የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥት መግቢያ

ላይ የተጣለ ድንኳን፣ ወዘተ የመሳሰሉት ነገሮች እያየን ጉዟችን ቀጠልን። የቀኑ ውሎችን ቤተሰብና ወዳጅ ዘመድ በመጠየቅ አሳልፈን መሸትሸት ሲል ወደ ማደሪያችን አዘገምን።

ከዚህ ቀጥለው ባሉ ቀናት፣ ሲሲኤን፣ ማርካቶ፣ የመከላከያ ዋና መስሪያቤት አከባቢዎች፣ ልደታ፣ መገናኛ፣ የጦር ኃይሎች አከባቢ፣ ሜክሲኮ፣ ቦሌ፣ ወዘተ የተባሉ አከባቢዎች እየዞርኩኝ ነበር ያሰስፍኩት። በነዚህ ቀናት ታዲያ የአዲስ አበባ ህዝብ በርግጥም ኑሮ እንደተወደደበት የሚያሳዩ በርካታ አጋጣሚዎች ገጥመውኛል። በዋናነት ከዚህ በታች ያሉት ጠቅሼ ኑሮ ከተወደደበት ህዝበ ጋር የነበረኝ ቆይታ ልቋጭ፡ -

- ከዚህ በፊት እማውቃት መርካቶ፣ በ10,000 ብር ሻንጣ ሙሉ ልብስና ሌሎች ለግል የሚያስፈልጉ መገልገያዎች ይዘህ የሚወጣባት ነች። በአንፃሯ አሁን ያለችው መርካቶ ያንን ብር መሸመት የሚችለው ትንሽየዋን ፌስታል እንኳን አትሞላም። ከ400 — 500 ብር ይሸጥ የነበረው ሱሪ አሁን ከ1400 — 1800 ብር፤ ከ150 — 200 ብር ይሸጥ የነበረው ቲ - ሸርት አሁን 800 — 1000ብር፤ ወዘተ ነው እሚሸጠው። ከዚህ በፊት በጅምላና በደርዘን ካልሆነ ሱቃቸው በር ላይ እንኳን ስትቆም ይጠየፉህ የነበሩ ጅምላ ነጋዴዎች፣ አሁን አንድም ሱሪ ልትገዛ ስትገባ ጠብ እርግፍ ብለው ያስተናግዱሃል። እነዚህ የንግድ እንቅስቃሴው እንዴት እንደተቀዛቀዘ ከማሳየቱም በላይ የከተማዋ ነዋሪ እንዴት ኑሮ እንደተወደደበት ያሳያል!!
- በየሆቴሉ ስትገባና የሆነ አገልግሎት ከተጠቀምክ በኋላ የሚመጣው የክፍያ ደረሰኝ ልብን ወከክ አድርጎ ህሊናን ያስታል። እኔና የእህቴ ባለቤት አንድ ኮፊ ሃውስ አረፍ ብለን ሁለት ቡና አዘዝን፣ ሂሳብ ብለን መቶ ብር ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥንላችሁ። አስተናጋጇ ሁኔታችን ገብቷት ደረሰኝ አስቀርጣ መጣችና ለናየው 145.51 ብር ይላል! ለምን ብሎ መጠየቅ አይቻልምና ከፍለን የአዲስ አበባ ነዋሪ እንዴት በኑሮ ውድነት እየተቀጣ እንዳለ እየገረመን ከቤቱ ወጣን!!
- የመንግስት ሰራተኛው የደሞዝ ጭማሪ ካገኘ ዓመታት ተቆጥሯል። አሁን ያለው የዋጋ ግሽበት ይህን የህብረተሰብ ክፍል ምን ያክል እየተሰቃየ እንዳለ ለመረዳት አይከብድም። ወንድሜ የመንግስት ሰራተኛ በመሆኑ፣ አብረውት የሚሰሩ የመንግስት ሰራተኞች ኑሮውን እንዴት እየገፉ እንዳሉ ጠይቄው ነበር። የመለሰልኝ መልስ እጅግ አሳዛኝም የአገሪቱ ውድቀትም እሚያሳይ ነበር። “መስረቅ የሚችል ይሰርቃል፣ የማችል ደግሞ እራቱን የ10 ብር ቆሎ ገዝቶ ይገባል” የሚል ነበር። ያገኘሁዋቸው የመንግስት ሰራቶኞች ተመሳሳይ ይዘት ያለው መልስ ነበር የሰጡኝ። በተለይ ለሙስና የተመቹ የስራ መደቦች ላይ የተመደቡ ሰራተኞች፣ ህጋዊ በሚመስል አኳኋን በግልፅ ሙስና ይጠይቃሉ ይቀበላሉ። እንዲህ በመሰለ ሁኔታ የሚተዳደር የከተማዋ ነዋሪ በእውነትም ኑሮ እንደተወደደበት ለመገንዘብ ጠንቋይ መሆን አይጠይቅም።

- በዘመነ ኢህአዴግ ህንፃዎች እንደ እንጉዳይ በየቀኑ እና በየሰፈሩ ይበቅሉ እንደነበሩ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። በዛን ብልጥግናዎች ጨለማ ነበረ የሚሉት ጊዜ ተጀምረው፣ 'ብሩሁ የብልግና ዘምን .... ኪኪኪ'¡¡ ደርሶባቸው በቁም የቀሩ ህንፃዎች በርካታ ናቸው!! የዛሬ ዓመት ያየሁዋቸው የተጀመሩ ህንፃዎች አሁንም እንዲሁ እንደተገተሩ አሉ። ምክንያቱ የግምባታ ግብዓቶች እጥረትና የዋጋ ግሽበት እንደሆነ አንድ በዘርፉ ተሰማርቶ ይሰራ የነበረው ጓደኛየ አውግቶኛል። በግምባታ ስራዎች ተሰማርተው የነበሩ አብዛኃኛው ተቋራጮች ከብልፅግና ጋር ንክኪ የሌላቸው ፍቃዳቸው መልሰው ስራ አቁመዋል፤ በነዚህ ተቋማት ስር ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩ ቋሚና የቀን ሰራተኞች ተበትነው ቤት ተቀምጠዋል ወይም የስራ መስክ ቀይረዋል። ይህን ሁኔታ ሳይ እውነትም የአዲስ አበባ ህዝብ እጅግኑ ኑሮ እንደተወደደበት ለመገንዘብ ችያለሁኝ!!
- የአዲስ አበባ ህዝብ ከዚህ በፊት ብሄርህ፣ የፖለቲካ አቋምህ፣ እምነትህ የፈለገ ቢሆንም ድጋፍ ስትጠይቅ ማንም ሰው የቻለውን ሁሉ ይደግፍ እንደነበረ አስታውሳለሁኝ። በዚያን ወቅት ኑሮ ሲወደድብህ፣ ህብረተሰቡ በሚሰጠው ድጋፍ ችግርህን ትወጣ ነበር። አሁን የከተማዋ ነዋሪ እጅግኑ በብሄር፣ በፖለቲካ አመለካከት እና እምነት ብትነትኑ ወጥቷል!! በችግር ብትጠበስ እና ደጅ አፉ ሂደህ ብትንፈራፈርም ዞር ብሎ የሚያይህ ሰው የለም!! መረዳዳት በከተማዋ ነዋሪዎች መካከል ፈፅሞ ጠፍቷል!! ይህንን ስትመለከት በእውነትም ኑሮ እንደተወደደበት ደረትህን ነፍተህ መመስከር ይቻላል!!
- አዲስ አበባን ጨምሮ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተጋሩ እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ ተጋሩ ትግራይ ላይ የተፈፀመውና እየተፈፀመ ካለው ጀኖሳይድ ተግባር አካል ሆነው እንደተያዙ ብሎም ጀኖሳይድ እንደተፈፀመባቸው በርካታ ሪፖርቶች አመላክተዋል!! አብዘሃኛወቹ እነዚህ ተጋሩ ከሳምንታት እስከ ወራት በማጎሪያ ካምፖች ታስረዋል!! የንግድ ተቋማታቸው ተዘግተዋል!! ከሥራ ገበታቸው ተፈናቅለዋል!! በህገ ወጦች ንበረታቸው ተዘርፈዋል!! በተለያዩ ሥፍራዎች ህይወታቸው አጥተዋል!! ወዘተ። ይህ የጀኖሳይድ ተግባር አሁንም በተለያዩ የሀገሪቱ አከባቢዎች እየተፈፀመ ይገኛል!! ሲቪል፣ የመከላከያ ኣባላት እና የፖለቲካ ፓርቲ አባላ የሆኑት ተጋሩ በማንነታቸው ብቻ በርካታ ወንጀሎች ተፈፅሞባቸውል!! <u>**እነዚህ ተጋሩ፣ አንድም እንደ ህዝባቸው የትግራይ ህዝብ መኖር ተወደባቸው በሌላም በኩል ደግሞ እንደ አዲስ አበባ ነዋሪዎች ኑሮ እንደተወደደባቸው ታዘብኩኝ!!**</u> የደጋ ሰው ቆላ ወርዶ ማሰር ይቀርና መኖር እንዴት እንደሚከብደው ግልፅ ነው!! መሀል አገር የሚኖሩ ተጋሩ አዋሽ አርባ፣ ሰመራ፣ ምዕራብ አባያ፣ ቤንች ማጂ ወስዶ እንዲታሰሩ ማድረግ የሞት ፍርድ መፍረድ መሆኑ የማይካድ ሃቅ ነው!! ይሁንና የዘር ማጥፋት አዋጁን በተጋሩ ያወጀው መንግስት፣ የመግደል ጥሙን ስላልረካ አሁንም በርካታ ተጋሩ በነዚህ ስከብት ማደሪያ እንኳን የማይመጥኑ የማጎሪያ ካምፖች መኖር ተወደባቸው እየተሰቃዩ ይገኛሉ። በቅርቡ የተለያዩ የውጭ መገናኛ አውታሮች እየዘገቡት ያለው ዘገባም ይህን ሃቅ የሚያረጋግጥ ነው!!

በአጠቃላይ የመሀል ሀገር ሰው በተለይ ደግሞ የአዲስ አበባ ህዝብ ኑሮ እንደተወደደበት በማያወላዳ መናገር ይቻላል፡ ፡ ይሁንና መኖር ከሚወደድብህ ኑሮ ቢወደድብህ ይሻላል የሚል እምነት አለኝ!! ኑሮ ሲወደድብህ በባለ 5 ኮከብ ሆቴል ትገለገል ከነበርክ ወደ 4 ኮከብ፣ ከ4 ወደ 3 ኮከብ፣ ከ3  ወደ 2 ኮከብ፣ ወዘተ የሆቴል አገልግሎት ትወርድ ይሆናል እንጂ መኖር አይወደድብህም!! ኑሮ ሲወደድብህ ከአሮስቶና ተከታይ ወደ ክትፎና ደረቅ ጥብስ፣ ከክትፎና ደረቅ ጥብስ ወደ ባለመረቅ ጥብስ - ቀይ ወጥና ቀቅል፣ ከቀይ ወጥ ወደ እንጀራ ፍርፍር፣ ከእንጀራ ፍርፍር ወደ ሻይ በዳቦና ሙዝ በዳቦ፣ ወዘተ ትወርድ እንደሆነ እንጂ የመኖር ሥጋት አይኖርብህም!! ኑሮ ሲወደድብህ ከዊስኪ ወደ ቢራ፣ ከቢራ ወደ ድራፍት፣ ከድራፍት ወደ ጠላ፣ ወዘተ ልትወርድ ትችላለህ እንጂ መኖር አይወደድብህም!! ስለዚህ መኖር ከሚወደድብህ ኑሮ ቢወደድብህ እጅግ የተሸለ ነው!!

እነዚህ ከላይ የገለፅኩዋቸው ትዝብቶች በህሊናየ እያሰላሰልኩኝ እና የቆይታ ጊዜዮን ስለጨረስኩኝ፣ መኖር ወደ ተወደደበት ህዝብ ለመጓዝ ሻንጣዮን ሸክፌ በጥዋቱ ቦሌ አየር ማረፍያ ተከሰትኩኝ!! የመመለሻ ቀኔ ዋዜማ ከወለየው የልብ ወዳጄ ሲ. መ. እና ሌሎች ወዳጅ ዘመዶች የስንብት ጣፋጭ ጊዜ ባሣሳለፍበት ምሽት የደረሰኝ የኢሜይል መልእክት ከፈትኩኝ፡፡ መልእክቱ የአየር ትኬት እዝል ሲሆን፣ አየር ማረፍያ መገኛ ጊዜ ከጥዋቱ 2፡30፣ አውሮፕላኑ የሚነሳበት ከቀኑ 6፡30 እና መቐለ የሚያርፍበት 7፡30 ሰዓት እንደሆነ ያሳያል!! በተጨባጭ የሆነው ግን የመነሻ ሰዓቱ ወደ 7፡50 ከፍ ብሎ የመድረሻው ሰዓት ደግሞ 9፡55 ነበር!! እንደዚህ ዓይነቱ የጊዜ ልዩነት አይቼም ሰምቼም አለውቅም እና ለጊዜው ግርምት ፈጥሮብኝ ነበር!! በተባለው ሰዓት አየር ማረፍያው ስደርስ ግን ምክንያቱ ገባኝ!!

የያዙኩት 2 መካከለኛ ሻንጣዎችና የላፕቶፕ ቦርሳ ወደ ሚገፋ ጋሪ ሰቅየ፣ ዓለም ዓቀፍ በረራዎች በሚያስተናግደው በር በኩል ዘለቅኩኝ፡፡ የተለመደውን በስካነር የሚታገዘውን የመጀመሪያ የፍተሻ ጣብያ ከተፈተሸኩኝ በኋላ ወደ ቀጣዩ ፍተሻ ስሄድ አንድ የኤርፖርቱ ሰራተኛ ወዴት እንሆንኩኝ ጠየቀኝ፡፡ መዳረሻየ መቐለ እንደሆነ ስነግረው፣ የመቐለ በረራ ተሳፋሪዎች የሚሰባሰቡበት የተለየ ስፍራ እንዳለ ነግሮኝ እየመራ ወሰደኝ፡፡ ስሜን፣ የስራና የቀበሌ መታወቅያየን ተጠይቄ እንዲሁም ስሜን ተናግሬ እና መታወቂያዎቼን አሳይቼ ከመቐለ ተሳፋሪዎች ተቀላቀልኩኝ፡፡ አጠቃላይ ተሳፋሪው ስቆጥረው 32 ቢሆንም፣ አንድ የተሳፋሪዎች ዝርዝር የያዘ ሰራተኛ ለሌላው ሰራተኛ ሁሉም 34ቱ ተሰፋሪዎች እንደገቡ ሲገልፅለት ስለሰማሁኝ አጠቃላይ ተሳፋሪው 34 ሰው እንደሆነ ተገነዘብኩኝ፡፡ ከዚህ ውስጥ 18ቱ የውጭ ዜጎች ሲሆኑ፣ የተቀረነው የአገሬው ሰዎች ስንሆን 11 ተጋሩና 5 የሌላ ብሄር ስለመሆናቸው እርስ በርስ በምንነጋገርበት ወቅት ተረዳሁኝ፡፡ ከጥዋቱ 2፡30 ተጀምሮ የጠበቀኝን የ5 ሰዓታት ፍተሻ እስከ ቀኑ 7፡50 ቀጠለ፡፡ ለውጭ ዜጎቹ የሚደረግላቸው ፍተሻ ቀላልና ከ 3 — 4 ደቂቃ የማይበልጥ ሲሆን፣ የአገሬው ሰዎች ግን እጅግ ከባድና 15 — 20 ደቂቃ የሚወስድ ነበር፡፡ የሚስጥር ኪስህ፣ ኮሌታህ፣ የገንዘብ መያዣ

ቦርሳህ ጨምሮ እያንዳዱ የያዝከው ሻንጣ እና እያንዳንዷ የሻንጣው አካል ይቦረቦራል ይፈተሻል!! የተቋጠሩ ፌስታሎች እየተዘረገፉ ድብልቅልቃቸው ይወጣል!!

የሚታይና የሚዳሰ እያንዳንዱ ንብረትህ ድብልቅልቁ ወጥቶ ከተፈተሸ በኋላ፣ ሁለተኛው ዓይነት ፍተሻ ይጀመራል!! በዚህ የፍተሻ ዓይነት በቦርሳህና ክስህ ያለችው ብር እንድታወጣ ትታዘዛለህ!! ያለችህን ብር አውጥተህ ካስረከብክ በኋላ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት ጊዜ ይቆጠራል!! በመሀል መሳሳት የሚባል አለና የቆጠራ ዙረ ይቀጥላል!! ከተፈቀደው በላይ ከተገኘ እዛው ለማንኛው ፈታሽ ትሰጠዋለህ ወይም ውጭ የሚጠብቅህ ሰው ካለ ለወዳጅ ዘመድ ትሰጠዋለህ!!

ሁለቱም ዙር ፍተሻ ከታለፈ በኋላ ሦስተኛው ዓይነትና ለጊዜው ድጅታል ብየ የሰየምኩትን የፍተሻ ዓይነት ይከተላል!! ድጅታል ፍተሻው የሚመለከታቸው ንብረቶች ላፕቶፕ፣ ታብሌት፣ ሞባይል እና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ንብረቶች ናቸው!! እያንዳንዱን እቃ በየተራ ታወጣለህ፤ ፓስዋርድ ትጽፋለህ፤ ለምትጠየቀው ጥያቄ ትመልሳለህ!! እንደዚህ ዓይነቱ ፍታሻ ከህግ አንፃር ሲታይ ምን ሲባል እንደሚችል ባይገባኝም የድርጅትህና የግልህ ሚስጢር ካለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ በጉልበት ሲበረበር ያሳዝናል!!

ወደ ዓራተኛውና የመጨረሻው ዓይነት ከመሄዴ በፊት፣ ተራው ደርሶኝ አንድ የአራዳ ልጅ የሚባል ዓይነት ወጣት ሻንጣዮን ይዤ ቀረብኩኝ! አብዘሀኛው በሻንጦቹ የሸከፍኳቸው እቃዎች የተወሰኑት የግሌ ቢሆኑም ኣብዛሀኛዎቹ ከጓደኞች፣ ዘመዶችና በርካታ ከማላውቃቸው ተጋሩ ለቤተሰቦቻቸው አድርስልን ብለው የሰጡኝ ንብረቶች ናቸው። ቡና፣ በርበሬ፣ ልብስ፣ ጫማ፣ መድኃኒቶች፣ ወዘተ ዓይነት እቃዎች በሻንጣዎቹ ተቸክፈዋል!! ሁሉም ስም ተፅፎባቸው በተለያዩ ፌስታሎች ታሽገው የነበሩ ቢሆኑም፣ እየተዘረገፉና እያንዳንዳቸው እየታዩ ሻንጣው ላይ ተዘረገፉ!! የአራዳው ልጅ ሁሉም እያየ ለማን እንደሆነ ይጠይቀኛል፣ እኔም የመጣልኝ መልስ እሰጠው ነበር። አሁን ሳስበው አስቂኝ ሆኖ ያገኘሁት መልስ ግን መድኃኒቶቹ የሚመለከት የሰጠሁት መልስ ነው!! የሳምባ ምች ክኒኑና መርፌው፣ የቆዳ በሽታ ቅባቱ፣ የኩላሊት ፈውሱ፣ የስኳር በሽታ ኢንሱሊኑና ክኒኑ፣ የደም ግፊት ማስታገሻው፣ የኮሉስትሮሉ ታብሌት፣ ወዘተ መድኃኒቶቹ አንድ በአንደ እያወጣ የማን ነው እያለ የአራዳ ልጁ ይጠይቃል፣ እኔም የራሴ ስል እየመለስኩኝ ነበር! እግዚሄር ያሳያችሁ፣ ይህ ሁሉ በሽታ የተሸከመ ሰው እንዴት ቁሞ ይሄዳል ብሎ ልጁ ቢጠይቀኝ ምን እንመልስለት እንደነበር አላውቅም!! ደግነቱ የአራዳ ልጁ መጠየቁን እንጂ እየሰጠሁት ያለውን መልስ ጉዳዩ አልነበረም!!

ልጁ አብጠርጥሮ ከፈተሸ በኋላ ግን ከየት መጣች ሳትባል፣ የአራዳ ልጆች ሰገጤ የሚልዋት ዓይነት ልጅ አጠገቤ ተከሰተች!! ልጁ የያዝኩት ብር ቆጠራ ላይ ተጠምዶ እያለ፣ ልጅቷ ትክሻየን ነካ አደረገችኝና ሻንጣውን እንድከፍት አዘዘችኝ!! እምቢ ማለት አይቻለምና አንዱን ሻንጣ ከፈትኩላት!! ተበታትኖ የነበረውን ንብረት አንዱን አንስታ ሌላውን እየጣለች ይባስኑ ትርምስምስ አደረገችው!! ሁለተኛው ሻንጣ ከመክፈቴ በፊት ግን እግዚሄር ይስጠው የአራዳ

ልጁ ቀጠሬው ጨርሾ፣ ተይ ፈትሸዋሎሁ ሲል ድምፁ አሰማ!! ተመስገን ያስብላል! በርካታ ተሳፋሪዎች መልሱ የተባሉት ንብረት ውጭ ለሚጠብቁዋቸው ሰዎች አድርሰው እየተመለሱ ባይም፣ እኔ ግን እድሜ ለአራዳ ልጁ ሁሉም ንብረቴ ይዤ ክብደት ወደ ሚመዘንበት ክፍል ሄድኩኝ!! ሻንጣዎቹን አስመዝኜ፣ በስካኒንግ ማሽን ወደሚታገዘው ዓራተኛውና የመጨረሻው ዓይነት ፍተሻ ጣብያ ሄድኩኝ!! እሱን ካለፍኩኝ በኋላ ትንሽ ማረፍያ አፈላልጌ በተሳፋሪዎች መቆያ ካሉ በአንዱ ሬስቶራንት በሬፍ በመቀመጥ ባስቸኳይ የሚበላ ነገር ቀማመስኩኝ!! ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ እንድንሳፈር ጥሪ ስለተደረገ፣ የመሳፈሪያ በረን አልፌ ወደ አውሮፕላንዋ በሚወስደው አውቶቡስ ተሳፈርኩኝ!! ከአውቶቡሱ እንደወረድኩኝ አውሮፕላኑ መያዝ ከሚገባው የሰው ብዛት እጅግ ያነሰ ተሳፋሪ ስለያዘ፣ አምስተኛው ረድፍ ላይ ካለው የአውሮፕላኑ መስኮት ለብቻየን ተቀመጥኩኝ!!

የተወሰኑ ደቂቃዎች አውሮፕላንዋ ውስጥ ከተቀመጥን እና የበረራ አስተናጋጆቹ የተወሰነ ማብራርያ ከሰጡን በኋላ፣ “አንዳልበር እንደ አሞራ ሰው አድርጎ ፈጥሮኛል” የሚል የአማርኛ ተረት ፉረሽ የሚያደርገውን የሰማይ ላይ በረራ ጀመርን!! ጉዞ ኑሮ ከተወደደበት ወደ መኖር የተወደደበት ህዝብ በእንዲህ ዓይነት መልኩ ጀመርነው!!

መኖር ከተወደደበት ህዝብ መካከል እና ፅናትና ትእግስት መገለጫው ከሆነው የትግራይ ህዝብ መካከል ሁኜ የታዘብኩትና አዲስ አበባ ከመሄዴ በፊት ያጋጠሙኝ ነገሮች በቀጣይ ክፍል አጋራሎሁኝ!!!

በሁለተኛው የፅሑፉ ክፍል እስክንገናኝ ሰላም ሰንብቱልኝ!!

ወዲ ረታ<br>ከእንዳ ሥላሴ ሽረ<br>21/10/2014ዓም